# የቱ ነው መንገዱ?

(ከግሀሉ በቀለ - ቶሮንቶ)

አላዋጣም ካለ፣ በሠላም መሄዱ
ወጋቢስ ከሆነ፣ ሽምግልና ፍርዱ
የማይቀር ከሆነ፣ መንግሥት መወንበዱ
ከግብ የሚያደርሰው፣ የቱ ነው መንገዱ?

ጠመዝማዛው መንገድ፣ አድካሚ አሰልችው
ብረትን አስወራጅ፣ ዝናርን አስፈችው
አንጀትን የሚያጥፍ፣ ልብን የሚሰብር
ጉልበት የሚያላላ፣ አንጎል የሚነዝር
ምነው እሩቅ ሆነ፣ አልደ'ረስ አለ
ሚስጥሩን ጉዳዩን፣ የሚያውቅ ሰው ካለ
ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ ቢናገር ምን አለ?

ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ ካልተናገረ ሰው
መረረኝ ሰለቸኝ፣ ብሎ ካልጮኸ ሰው
ሥርዓቱ ይቀየር፣ በቃኝ ካላለ ሰው
ሠላማዊ ባርያ፣ መሆን ካስደሰተው
እንደምን ሆኖ ነው፣ ነፃነት የሚገኘው?

'ሚሰማ ከጠፋ፣ የሚደርስ ወዳጅ
ድምፅን ማለስለሱ፣ ካልሆነ የሚበጅ
መሆን የለብንም፣ ሞፈር አስቀራጭ
መጋተር ብቻ ነው፣ ያለን አማራጭ፡፡

ይቆረጥ የለም ወይ፣ ከሞኝ ደጅ ሞፈር
ይቆረስ የለም ወይ፣ የምስኪን ሰው አፈር
ይወሰድ የለም ወይ፣ ወርቅና ምርጥ ዘር
ተሚጋች ሲጠፋ፣ ላገር 'ሚቆረቆር፡፡

እይታህን አጥራው፣ተባበር ወገኔ
ተሚገት ተጋተር፣ በኢትዮጵያዊ ወኔ
ለጥልያን አልወደክ፣ እንኳን ለወያኔ!

ጊዜ ያለለት ቅል፣ ድንጋይን ይሰብራል
እሱም ጊዜው ሲደርስ፣ በአፈር ይበላል
እንዳለ የሚቆይ፣ ምንም ስለሌለ
የወያኔም ውድቀት፣ በቅርብ ይታይ የለ
ባንድነት ከቆምን፣ ትግሉ ከቀጠለ፡፡

ድንቅ አድርጎ የሰራት፣ ውቧ አገራችን
ጨዋና ጅብደኛው፣ ታጋሹ ህዝባችን
ዓለም ያስተዋለው፣ አኩሪው ታሪካችን
በፀረ ህዝብ መንጋ፣ ሲታረስ ቤታችን
ተቆራርሶ ሲሸጥ፣ ድንበር ወሰናችን
ትርጉም አልባ ሲሆን፣ እንዲህ መኖራችን
የችግሩ መፍቻ፣ ይሁን ትግላችን፡፡

ወያኔ የሚባል፣ ዘረኛ ድርጅት
መለስና አዜብ፣ በረከት ስብሀት
አገር የሚያጠፉ፣ ወፈፌ ፍጥረታት
አይበጁንም ይቅሩ፣ እንጦርጦስ ይውረዱ
ይኸው ነው ዳኝነት፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ፍርዱ፡፡

ነፃነት ፍለጋ፣ ጫካ የገባ ሰው
አሸናፊ ሆኖ፣ሥልጣንን ሲይዘው
ኸረ ለምንድነው፣ ማስተዋል የሚያጣው
የገዛ አገሩን፣ የሚወጋው የሚያደማው፡፡

እንዲህ አይነት፣ መንግሥት ከሚገዛን ከቶ
ይውጣ ጀግንነቱ፣ ሚናችን ለይቶ፡፡

እራሱ የሚከስ፣ እራሱ የሚያስር
እራሱ የሚዳኝ፣ ካገር የሚያባርር
ፍርደ ገምድል ዳኛ፣ የዘመኑ ንጉሥ
የወያኔ ቁንጮ፣ ክቡር አቶ መለስ
በለኮሰው እሳት፣ መለብለቡ አይቀርም
የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንባ፣ እንዲህ ፈሶ አይቀርም፡፡

አምባ ገነንነት፣ ለማንም አልበጀም
እንኳን ለዜናዊ፣ ለሂትለር አልሆነም
ታሪክ የሚያሳየን፣ ደግሞና ደጋግሞ
ይህንን ሐቅ ነው፣ እንደሀውልት ቆሞ፡፡

በምርጫ በቅርጫ፣ በቡጢ በጡጫ
በሠላም በትግል፣ በዝላይ በሩጫ
ነፃነታችንን እናስከብራለን
በታላቋ አገር፣ ኮርተን እንኖራለን፡፡

EthioLion.Com